

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም
ለማዕቱ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስን
ወደ ቤተ መቅደስ እንዲያስገባው ካህኑን እንደላከችለት



አንድ አምላክ በሚኾን በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አምነን የቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ዜና ዕረፍቱ ከሰማይ ለሊቀ ጳጳሱ አባ ቴዎፍሎስ እንደተነገረውና አባቱና እናቱም ቅድስት ዕረፍቱን እንደሰሙ የሚናገር በዕለተ እሁድ የሚነበብ የብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስን ዜና ገድሉን በእግዚአብሔር አጋዥነት እንጀምራለን ጸሎቱና በረከቱ ከእኛ ጋራ ይኹን ለዘለዓለሙ አሜን ::

፩. መጽሐፉንም በእጅ ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በትዕምርተ መስቀል አማትቦ አንገቱን ወደ ሰማይ እንደ አቀና ዐረፈ :: ያንጊዜም ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ::

፪. ጌታም ንጽሕት ነፍስ ሆይ ስለወደድኽኝ በሰላም ወደእኔ ነይ ብሎ በክንዱ አቅፎ ያዛት:: እርሱም በሠረገላ ኪሩቤል ተቀምጦ ነበር :: ማኅበረ መላዕክት ነቢያት ሐዋርያት ጻድቃንና ሰማዕታት ደናግልና መነኰሳት በዙሪያው ቆመው ሃሌ ሉያ እያሉ ያመሰግኑ ነበር:: ኹሉም

በዚህ ዓለም መከራ የተቀበለ ደስ ይለዋል ። ምስጋና ለእግዚአብሔር ይኹን እያሉ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስን ተቀበሉት ። በእልልታ በደስታ በምስጋና በዝማሬ ወደሰማያዊት ኢየሩሳሌም አገቡት ። የቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ዕረፍቱ በወርኃ ጥቅምት ዐሥራ ዐራት ቀን እሁድ በሦስት ሰዓት ነው።

፫. የብዙ ብዙ የሚኾኑ ቅዱሳን መላዕክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት እያሉ ሱራፌል መለከት እየነፉ ሊቃነ መላዕክትም እልል ሲሉ ቅዱሳን ነቢያት ሐዋርያት ሰማዕታት ሃሌ ሉያ እያሉ ሲያመሰግኑ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቴምፍሎስ ምስጋናቸውን እስኪሰማ ድረስ የመላዕክት የምስጋናቻው ድምፅ ያስተጋባ ነበር ።

፬. በዚችም ቀን ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ቴምፍሎስ ለቅዳሴ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳለ ከእርሱም ጋራ ቀሳውስት ዲያቆናት የቍስጥንጥንያ ሀገር ሕዝብ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቆመው ሳሉ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቴምፍሎስ ሆይ የታዘዝኸውን ስማ ። መሥዋዕትህ ይሠምር ዘንድ ወደ ንጉሥ ቤት ሒደህ የቅዱስ ገብረ ክርስቶስን ሥጋ አምጣ የሚል ቃል ከሰማይ ሰሙ ። ይኸንንም ነገር

በሰሙ ጊዜ ከዚያ ቆመው የነበሩትን ኹሉ ፍርሐት ድንጋጤ ያዛቸው ። ያን ጊዜም ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ቴምፍሎስ በውኑ በአደባባይ ዛሬ የዐረፈ ለመንግሥተ ሰማያት የሚገባ ሰው አለን ። ስለ እርሱ የተነገረውን ቃል ከሰማይ ስምተናልና ብሎ ወደ ንጉሥ ቴምዶስዮስ ዘንድ ላከበት ።

ጅ. ንጉሡ ቴምዶስዮስም አገልጋዮቹን ለመንግሥተ ሰማያት የተገባ እንደኾነ እናንተ የምታውቁለት ዛሬ የዐረፈ ሰው በእኔ ግቢ አለን አላቸው ። ጌታችን እኛስ አላወቅንም አሉት ። ንጉሡም እንግዲያስ ሒዱ በጥብቅ መርምራችሁ ተረዱ አላቸው ። ከዚህ በኋላ እነዚህ ኹለት አገልጋዮች መጥተው በንጉሡ ፊት ቆመው ጌታችን ሆይ ያ አንተ አደራ ያልኸን ድኃ ከእኛ ዘንድ አለ ። እርሱ ለመንግሥተ ሰማያት የተገባ እንደኾነ እኛ ምሥክሮቹ ነን ። እርሱ ጡት ማታ አንተ ትልክለት የነበረውን ምግብ እንደሚበላ ተቀብሎ ሰው ሳያየው ለነዳያን መጽውቶ እሱ ግን ሌትም ቀንም ይጸም ነበር ደግሞም አገልጋዮችህ ኹሉ ሲሰድቡት ሲደበድቡት ሲያሠቃዩት ክፉ ሲውሉበት ይኸን ኹሉ ይታገሥ ነበር ።

፮. ንጉሥ ሆይ አሁንም ሔደን እንየው አሉት ንጉሡም በቶሎ ሒዳችሁ እዩት አላቸው። እነርሱም በሔዱ ጊዜ ብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ዐርፎ አገኙትና ይህንኑ ለንጉሡ ነገሩት ።

፯. ያን ጊዜም ንጉሡ ከሰማይ የተነገረህ ቃል እውነት ነው ። እነሆ በእኔ ግቢ ዛሬ የዐረፈ የእግዚአብሔር አገልጋይ ተገኝቷል ብሎ ወደ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቴዎፍሎስ ዘንድ ላከበት ።

፰. ሊቀ ጳጳሳቱም አባ ቴዎፍሎስም በቀሳውስት በዲያቆናት ቍጥር ልክ መስቀል ማዕጠንት መጽሐፍ ይዞ የቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ሥጋ ከአለበት ዘንድ ወደ ቤተ መንግሥት ሔዱ ። ንጉሡም ሊቀ ጳጳሳት ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስት ዲያቆናት በሚቀመጡበት ቤት ውስጥ የብር የወርቅ ወንበሮች አዘጋጀ ። ብርሃኑ እንደ ፀሐይ እስኪሸን ድረስ ብዙ መብራቶችን አደራጀ ንጉሡና ሊቀ ጳጳሳቱ ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት የከበረ ሥጋውን የዩ ዘንድ ብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ። ወደነበረባት ዳስ ገቡ ። በእጁ

የጨበጠውን ደብዳቤ አዩ ። ደብዳቤውንም ከእጁ ሊያላቅቁ ወድደው ነበር ። ነገር ግን ንጉሡም ቀሳውስቱም ደብዳቤውን ከእጁ ማላቀቅ አልተቻላቸውም። ሊቀጳጳሳቱም አባ ቴዎፍሎስ ልጆቼ ሆይ ተነሡ ። በቅዱሱ ሥጋው ፊት እንጸልይ አለ ። መላልሰው ጸለዩ። ጸሎታቸውንም ከጨረሱ በኋላ ሦስት መቶ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እያሉ ብዙ ጸሎተ ምሕላን አደረሱ። ያን ጊዜም በእግዚአብሔር ፈቃድ የብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ እጅ ተዘረጋ ። ሊቀ ጳጳሳቱም ቀርቦ በንጉሡ ልጅ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ እጅ ውስጥ የነበረችውን ያቺን ደብዳቤ አንሥቶ አንብቦ በተረዳ ጊዜ ምርር ብሎ አለቀሰ ።

፱. አንብቦ ከጨረሰ በኋላም ደብዳቤዪቱን ለንጉሡ ሰጠው ። እርሱም ተቀብሎ በአነበባት ጊዜ የተወደደ ልጁ እንደሞነ ዐወቀ ። ያን ጊዜ ከመሬት ላይ ወድቆ በአመድ ላይ እየተንከባለለ ፊቱን እየመታ የአልጋዬ ወራሽ ያልኩህ በደስታ በፍቅር ያሳደግኹህ ጥበብን ሥነ

ሥርዓትን ያስተማርኹህና የዐይኔ ብርሃን ልጄ ወዳጄ በልጅነትህ በአንተ ደስ ብሎኝ ነበር። በጐለመስኽ ጊዜ ግን አሳዘንከኝ ። ደስታዬን ለወጥኽ ። ልቤንም አቃጠልኻት። ደም ግባቴንም አጠወለግኸው አንተ እኔን አባትህን ስታውቅ መከራውን ታገሥኽ ራስህን ድኃ አደረግህ ። ዐሥራ አምስት ዓመትም ከአባትህ አደባባይ ወድቀህ ኖርኽ ። የአባትህ ባሮች ሲሰድቡህ ሲደበድቡህ የወጭቱን እጣቢ በላይህ ላይ ሲያፈስሱብህ ታገሥኽ እያለ መራራ ልቅሶን አለቀሰ ።

፲. እናቱ ንግሥት መርኬዛም በሰማች ጊዜ እንደ እብድ ኾና ደረቷን በድንጋይ እየደቃች ፊቷን እየመታች ጠጉሯን እየነጨች እየሮጠች መጣች ። ወዳለበትም ገብታ በላይ ላይ ወድቃ ሥጋውን አቅፋ በለመንኹት ጊዜ እግዚ አብሔር አንተን የሰጠኝ የዐይኔ ብርሃን ልጄ ሆይ ሚስት እስከአመጣሁልህ ጊዜ ድረስ በአንተ ደስ ብሎኝ ነበር ። አንተ ደስታዬን መጽናናት ወደማይገኝለት ኀዘን መለስኸው። እግዚአብሔር አምላኬም አንተን እንዲያሳየኝ ተስፋ አድርጌ ደጅ ስጠና ተስፋ አልቈረጥኹም ነበር ።

፲፭. እግዚአብሔር ግን መታመኔን አይቶ ወደዚህ መለስህ ። አንተ ግን እያወቅህ ታግሠህ ኖርኽ በአደባባዬ እንደ ድኻ እንደ ምስኪን የተናቅህ የተጠላህ ኾነህ ወድቀህ ስትኖር ቸል አልኩህ አላወቅሁም ። አንተ ልጄ ወዳጄ ስትኾን በብዙ ጭንቅና መከራ ዐሥራ አምስት ዓመት አሳለፍኽ ። ልጄ ሆይ ከእንግዲህስ ወዲህ ለወለድኩህ ለእኔ ለእናትህ ወዮልኝ ። ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ለተሸከመችህ ማሕፀኔ ወዮላት ። ለታቀፉህ እጆቼ ላጠቡህ ጡቶቼ ወዮላቸው ። በፍቅርና ፍላፃ ለተወጋችው ልቤ እስከ ፍጻሜ ዘመን ወዮላት ። እስከ ዘለዓለም መጽናናት መጨረሻም የሌላት ኀዘን አግኝታኛለችና ለእኔ ወዮልኝ እያለች እየጮኸች አለቀሰች ።

፲፮. ሙሽራይቱ ሚስቱም ልብሷን እየቀደደች ፊቷን እየመታች መራራ ልቅሶ እያለቀሰች መጣች ። ጌታዬ የኑሮ ጓደኛዬ ከአንተ ጋራ በቤተ ክርስቲያን ሕግ ተክሊል አድርጌ ነበር። ግን በሚጉላ ቤት ትተኸኝ ሔድኽ ። በጎ ሥራ ለመሥራት ከአንተ ጋራ ቃል ኪዳን ስለገባሁ ሠላሳ ዓመት ብቻዬን ለኖርኹ ለእኔ

ወዮልኝ ። ኀዘን መልቶኛልና እንደ እሳትም አቃጥሎኛልና።

፲፫. አንተን የኑሮ ጓደኛዬን ያሳየኝ ዘንድም እስከዛሬ ሠላሳ ዓመት ሙሉ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት ። ደጅ ጥናቴንም ወደእንባና ልቅሶ መለሳት ። በመጋረጃ የምውል ሙሽራ ነበርኹ ዛሬ ግን አጋለጥኸኝ ። ትተኸኝ በመሔድህ ኀዘነተኛ ስኾን እነሆ የከበርኹ ሙሽራይት የነበርኹ እኔ እስከ መጨረሻው አውታታ ኾንኹ ። ባልንጀሮቼ የሮምና የቍስጥንጥንያ ልጅ አገረዶች ሆይ ኑ ለእኔ አልቅሱልኝ የኑሮ ጓደኛዬን ያሳየኝ ዘንድ በመታመን እግዚአብሔርን ደጅ ስጠናው ነበርሁ እንግዲህ ተስፋዬ ተቈረጠ ። ደጅ ጥናቴም ከንቱ ኾነች እንግዲህስ ወዲህ እንደየፈ መንጢጥ እኾናለሁ ያቺ የፈ መንጢጥ ባሏ በሞተ ጊዜ በጥፍሯ ፊቷን ነጭታ ምላሷን ሠንጥቃ ወደ ጫካ ሔዳ ብቻዋን ትኖራለች ።

፲፬. ሌላ ወፍ ወደእርሷ በመጣ ጊዜም ትጮኻለች ። በአጫጫኗም ባሏ የሞተባት ምላሷን የሠነጠቀች ኀዘነተኛ እንደኾነች ዐውቆ ትቷት ይሔዳል ። እኔም ከዛሬ ጀምሮ እንደ እርሷ እኾናለሁ እያለች ትጮኽ ነበር ።

፰. በእርሱ ላይ ክፉ የዋሉበት የንጉሥ አገልጋዮችም መጡ ። እኛ አገልጋዮች ስናሠቃይህ ስንበድልህ ኖረናልና ክፉም አድርገንብህልና ወዮልን ። እንደእኛ የበደለ ከእኛ በፊት ከእኛ በኋላ የለምና ወዮልን ። የእኛን ነገር ሰው ቢሰማው የተናቅን የተጠላን እንኾናለን ። ፈጽሞ ሰው የአላደረገው እኛ በአንተ ላይ ያደረግነው ብዙ ነገር አለ ። አንተስ እኛ አገልጋዮችህ እንደኾነ እያወቅህ ታገሥኽ እያሉ አለቀሱ ።

፱. በቊስጥንጥንያ ያሉ ኹሉ ንጉሥ የጠፋውን ልጁን እንዳገኘ ስለእርሱ ከሰማይ ቃል እንደተነገረ በሰሙ ጊዜ ይኸን የአዩ ዘንድ ሕዝብ ኹሉ መጡ ። በዚያችም ዕለት በንጉሡ ቴዎዶስዮስ ቤት የንጉሡ ልጅ በንጉሡ ደጃፍ ወድቆ ሳያውቁትም ሞቶ ስለተገኘ ጽኑ ልቅሶና ብዙ ዋይታ ተደረገ ።

፲. ዳግመኛም የብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ሥጋውን ስለአገኙ ፍጹም ተድላ ደስታ ኾነ ። በዚችም ዕለትም ብዙዎች

ድውያንና ዕውራን ሐንካሳን መጡ ። ሥጋውን እየዳሠሡ ሣጥኑን በተሳለሙ ጊዜም ፈጥነው ተፈወሱ ። ኹሉም ከደዌያቸው ዳኑ ። በዚያም ብዙ ግፊያ ኾነ ።

፰. ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ቴምፍሉስና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስትና ዲያቆናትም ሥጋውን አንሥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊወስዱ ቢሀሱ ከግፊው የተነሣ መውሰድ ተሳናቸው ። ሊቀ ጳጳሳቱም ንጉሡን ወርቅና ብር አምጥተው በበሩ ፊት ለፊት በመንገዱ ላይ እንዲበትኑ አዘዘ ። ነዳያን ወደዚያ ወደ ወርቁ ሲሔዱ ያን ጊዜ ግፊያው ይቀላል። የቅዱስ ገብረ ክርስቶስንም ሥጋውን መው ሰድ እንችላለን አለው ። ንጉሡ ቴምዶስዮስም ሊቀጳጳሳቱ እንደ አዘዘ አደረገ ወርቅና ብር አምጥተው በተኑ ። ነገር ግን በብዙ ጭንቅ እየተጋፉ ወደቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ሥጋ ይሸቀዳደሙ ነበር እንጂ ወደወርቁና ብሩ የተመለሰ የለም። በጭንቅም የቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ሥጋውን ወስደው ወደ ቤተ ክርስቲያን አገቡት ።

፱፱. መሥዋዕቱን አዘጋጁ ። ሊቀ ጳጳሳቱም ቀድሶ ሕዝቡን አቈረባቸው ። እንደሕጉም ከፈጸሙ በኋላ የቅዱስ ገብረ ክርስቶስን ሥጋውን በንጹሕ በፍታ ገንዘው በሣጥን አድርገው በቤተ ክርስቲያን ቀበሩት ። በመቃብሩ ላይም ብርሃን ወረደ ። የብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ መቃብሩም ድውያንንና ሕመማንን ኹሉ የሚፈውስ ኾነ ።

፻. የብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ጸሎቱ ይደረግልን ። የፈጣሪው ረድኤትም ከእኛና ከሀገራችን ኢትዮጵያ ከወዳጆቹም ኃይለ ገብርኤልና ገብረ መድኅን ጋራ ከመላው ሕዝበ ክርስቲያንም ኹሉ ጋራ ይኹን ለዘለዓለሙ አሜን ።



ፅረፍተ ሥጋሁ ለቅዱስ ገብረ ክርስቶስ